የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
**UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)**

## ማን ያውራ የነበረ ፣ ማን ያርዳ የቀበረ
## የሕብረቱ የተዋጣለት ሕዝባዊ ስብሰባ በሎስ አንጀለስ

ባለፈው ሳምንት ሐሙስ ሰኔ 28 ቀን 1998 ዓ.ም. (Thursday, July 6, 2006) በሎስ አንጀለስ ከተማ ከፍተኛ ግንዛቤን ያስጨበጠ፣ የወቅቱን የአገራችንን የኃይል አሰላለፍ የመረመረና ሕዝባዊ ትግሉ መከተል ያለበትን የትግል አቅጣጫ በሚገባ ያመላከተ ሕዝባዊ ስብሰባ በሕብረቱ የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴዎች አማካይነት ተዘጋጅቶ በተሳካ ሁኔታ ተካሄዶአል። በስብሰባው ላይ በብዙ መቶዎች የተቆጠሩ አገርወዳድ ኢትዮጵያዊያን በቦታው ተገኝተው የተሳተፉ ሲሆን ጠቅላላ ስብሰባው በፓል ቶክ አማካይነት በመላው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያዊያን መከታተል ከመቻላቸውም በላይ ጥያቄያቸውን በማቅረብና በርካታ ገንቢ አስተያየታቸውን በመስጠት ለመሳተፍ እንዲችሉ ተደርጎአል።

በዕለቱ በተለይ በትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ ዙሪያ ያሉ ግልፅነት የጎደላቸውን ጉዳዮች በተመለከተ በኔዘርላንድ ባለፈው ግንቦት ሕብረቱን ወክለው የተገኙት አቶ አረጋዊ በርሄና ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ተፈጠረ የተባለው ትብብር ግልጽነት የጎደለው እንዲሁም ሕዝባዊና አገራዊ ጎዳዮችን ወደ ጠርዝ በመግፋት በመካሄዱ ከፍተኛ ጥርጣሬና ብዙ ጥያቄዎችን አስነስቶ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ካለመቻሉም ሌላ ትኩረት እንዲሰጥባቸው የቀረቡ ጥቆማዎችን ተፈጠረ የተባለው የትብብሩ መስራች ስብሰባ ለማስተናገድ ባለመቻሉ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት የሕዝብና የታሪክ ተጠያቂ ላለመሆን ራሱን ለማግለል እንደተገደደ ገልጸዋል። የትብብሩ መሥራች ስብሰባ ከተካሄደ ከአንድ ወር ተኩል በኃላም በአሁኑ ወቅት "ከአፈርኩ አይመልሰኝ" በሚል ዘይቤ ሕዝብን ለማደናገርና ለማሳሳት በደፈናው ደግፉ ከማለት በስተቀር ጥያቄ ያስነሱና ጥርጣሬን ያስከተሉት ጉዳዮች ዛሬም እንዳሉ መሆናቸውን አጋልጠዋል። በተቃዋሚነት የተሰለፉ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ በግልጽነት በሕብረት ቆመው የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ለመምራትና ለማገዝ በኢትዮጵያዊነት ጃንጥላ ሥር መሰባሰብ እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል። ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ዶ/ር ሥዩም ገላዬና አቶ መርሻ ዮሴፍ ተደራጅቶና ተጠናክሮ በጋራ መታገል የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑንና በቀጣዩ ምን መደረግ እንዳለበት ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ከአውሮፓ የመጡት የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባኤ ሰብሳቢ ዶ/ር ፀሐይ ብርሃነ ሥላሴም በሕዝባዊ ትግሉ ውስጥ የሲቪክ ድርጅቶች ያላቸውን ሚናና አጋዥነት እንዲሁም ተቻችሎና ተጋግዞ መጠነ ሰፊውን የአገራችንን ችግር ለመወጣት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

ተሳታፊዎችም የተለያዩ ጥያቄዎችን አቅርበው አጥጋቢ መልስና ማብራሪያ አግኝተዋል። ሕብረቱ የወሰደውን የአገርን አንድነት የማረጋገጥና የመከላከል እንዲሁም የሕዝብን ጥቅም የማስጠበቅ አቋም በመደገፍና በማድነቅ በርካታ ተሳታፊዎች የድጋፍ አስተያየት ሰጥተዋል። ሕዝብ ሚዛናዊ መረጃ ለማግኘት እንዲችል በተለይ ትብብር ለነፃነትና ዲሞክራሲ ተወካዮች ከሕብረቱ ተወካዮች ጋር በአንድ መድረክ ተገናኝተው ማብራሪያ ለመስጠት እንዳይችሉ ሕዝቡን በመከፋፈልና በማደናገር ከስብሰባ እስከ ሰልፍ ዝግጅት የተፈፀመው አሳዛኝ ድርጊት በአገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያኑ ተኮንኖ ለወደፊቱ ከመሰሉ ተግባር እንዲቆጠቡና እንዲታረሙ በአገራችን ስም በአጽንዖት ተጠይቆአል።

ተመሳሳይ ሕዝባዊ ስብሰባ በተከታታይ ኢትዮጵያዊያንኖች በሚኖሩባቸው በሰሜን አሜሪካ ዋና ዋና ከተማዎች ለማካሄድ እንደታቀደ የተገለጸ ሲሆን በቅርቡ በአትላንታ፣ በሲአትል፣ በዋሽንግተን ዲሲና በሌሎችም አካባቢዎች ለማካሄድ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸው ታውቆአል።

የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ኮሚቴዎች መድረክ
ሎስ አንጀለስ 3/11/1998 ዓ.ም. /**Los Angeles July 11, 2006**